## 4. የክልል ኮሚሽን

በጣሊያን የጥገኝነት ጥያቄዎን ለመመርመር ብቃት ያለው ብቸኛው አካል የክልል ኮሚሽን ለአለም አቀፍ ጥበቃ እውቅና ነው።


ጥያቄዎ ሚመረመረዉ ቃለ መጠይቅንም በመጠቀም ነዉ። በሂደቱ አስተርጓሚዉ የራስዎ ቋንቋ እና የራስዎ ጾታ ያማከለ እንዲሆን መጠየቅ ይችላሉ። ቃለ መጠይቅዎ በቪዲዮ የተቀዳ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጉዳይ ካልተስማሙ ኮሚሽኑ ጥያቄዎን ተረድቶ እንዲወስን ምክንያቶን መግለጽ ይችላሉ።

በሁሉም ደረጃዎች ግን በተለይ በዚህ ጊዜ ለጥበቃ ጥያቄዎ ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያምኑትን ሰነዶች፣ የግል አጭር መግለጫዎች፣ የህክምና የምስክር ወረቀቶች፣ ፎቶግራፎች ወይም ሌሎች ማስረጃዎችን የማሳየት እድል አለዎት።


የስደተኛ ሁኔታ (እዉቅና)


ንዑስ ጥበቃ

የክልል ኮሚሽኑ የጥገኝነት ሁኔታ ፣ 2ይ ደረጃ ጥገኝንት እዉቅና ወይም አሉታዊ ውሳኔ ማስተላለፋ ይችላል። በዚህ ሃላኛ ጉዳይ፣ ኮሚቴው አሁንም ለእርስዎ ተጨማሪ ጥበቃ በማድረግ ልዩ ጥበቃ ተብሎ የሚጠራው ጥበቃ ሊሰጥ ይ ችላል፣ ወደ ትውልድ አገርዎ ቢመለሱ ግን ለሕይወትዎ አደጋ ነው።


አሉታዊ ዉሳኔ

ልዩ ጥበቃ

በኮሚቴው በተወሰደው ውሳኔ ባልተስማሙባቸው ጉዳዮች ሁሉ ይግባኝ የማለት መብት አለዎት። እንዲሁም በጠበቃ በነጻ የመታገዝ መብት አለዎት።

## 5. የጥበቃ ተጠቃሚ መብቶች

ጥገኝነት መብት ካገኘህ እንደሁኔታው የሚለያይ የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት መብት አለህ፥ እነዚሁም የጥገኝነት ዓይነት አለምአቀፍ ጥገኝነት (ፖሊቲካል ኣሳይሉም) እና 2ኛ ደረጃ ጥገኝነት ሲሆኑ፣ የአምስት ዓመት መኖርያ ፍቃድ ያሰጣሉ፣ የሁለት ዓመት መኖርያ ፍቃድ ደግሞ ልዩ ጥገኝነት (ስፐሻል ፕሮተክሽን) ሲሆን ይሰጣል ጊዜው ሲያልቅ የመኖሪያ ፈቃድዎን እንዲታደስ መጠየቅ ይችላሉ። የመስራት፣ የመማር እና የህክምና እርዳታ የማግኘት መብት አሎት።




- ንዑስ ጥበቃ
- ንዑስ ጥበቃ




- ልዩ ጥበቃ

የስደተኛ ደረጃ ወይም 2ይ ደረጃ ጥገኝነት ዶክመንት ካሎት በአውሮፓ ውስጥ እስከ ዘጠና ቀናት ድረስ መጓዝ የሚችሉበትን ሰነድ መጠየቅ ይችላሉ።
ይህ ሰነድ ከትውልድ ሀገርዎ በስተቀር አውሮፓዊ ባልሆኑ ግዛቶች ውስጥም የሚሰራ ነው። ለማንኛውም፡ ከመሄዳቸሁ በፊት ሁል ጊዜ መሄድ በሚፈልጉት የአገሪቱ ኤምባሲን ይጠይቁ።
እንዲሁም፣ ቤተሰብን እንደገና ማገናኘት በሚባል አሰራር ቤተሰብዎን በህጋዊ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ጣሊያን እንዲመጡ የማድረግ መብት አለዎት።


የመስራት፣ የመማር እና የመታከም መብት አሎት።

ያስታውሱ፣ ስለማንኛውም የአሰራር ሂደት ስጋት ካለብዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ የሚስተናገዱበትን ማእከል ህጋዊ ኦፐሬተር፣ UNHCR፣ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲን ወይም ሌላ የታመኑበት የባለሙያ ጥገኝነት ድርጅትን ማነጋገር ይችላሉ።

Progetto co-finanziato dall'Unione Europea
MINISTERO DELL'INTERNO
FONDO ASILO, MIGRAZIONE E INTEGRAZIONE (FAMI) 2014-2020

UNHCR
The UN Refugee Agency

**scan to find information**

| HELP.UNHCR.ORG | TELEGRAM | JAMAMAP.IT |
| --- | --- | --- |
| asylum, rights and duties, and dedicated service | Opportunities, events,and dedicated service | Service mapin 19 lenguages |

**HELPLINE**
**800 905 570**
9:00 - 5:00 pm
From Monday to Friday
numeroverderifugiati@arci.it
Lycamobile +39 3427754946

**IN CASE OF EMERGENCY**
24/7 - free - confidential

| Police and Ambulance | Antiviolence Helpline | Antitrafficking Helpline |
| --- | --- | --- |
| 112 | 1522 | 800 290 290<br>LYCAMOBILE + 39342 775 4946 |

## ጥበቃ ያስፈልግዎታል?



## 1. የከውጭ አገር ወደ ጣሊያን የሚገቡት የባዕድ አገር ሰው መብቶች እና ግዴታዎች ምንድን ናቸው?

እንኳን ደህና መጡ ጣሊያን ደርሰዋል። ይህ ማለት እርስዎ በአውሮፓ ህብረት ውስጥ ነዎት ማለት ነው። ወደ ጣሊያን የሚመጣ ማንኛውም ሰው ማንነቱን ለመለየት ለሀገሪቱ ባለስልጣናት ሪፖርት ማድረግ አለበት። ፖሊስን ለማነጋገር አይፍሩ። እነሱ ሊረዱዎት እና ሊጠብቆት ይችላሉ።



ማን እንደሆኑ ለመለየት፣ ማንነትዎን ማሳወቅ አለቦት። የ ግል ስም ፣ የቤተሰብ ስም፣ የትውልድ ቀን ፣ የትወለዱበት ሀገር እንዲሁም ዜግነትዎን በትክክል እና በተሟላ ሁኔታ መግለፅ ያስፈልጋል። ሰነዶችም ካሉዎት በዚህ ጊዜ ያሳዩዋቸው።
ከቤተሰብዎ አባላት ጋር አብረው የሚጓዙ ከሆነ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። ከሀገርህ የወጣህበትን ምክንያት እና ጣሊያን የገባህበት ምክንያትን ማስረዳት በጣም አስፈላጊ ነዉ።
የመለየት ሂደት ሚጠናቀቀዉ ለሚመጡ ሰዎች አስቀድሞ በተዘጋጀዉ የፎቶ ምልክት ማድረጊያ ወይንም አሻራ በመዉሰድ ነዉ።




መግለጫዎችዎ በትክክል እንዲመዘገቡ የሚነገርዎትን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።
የሆነ ነገር ለእርስዎ ግልጽ ካልሆነ ወይም ጥርጣሬ ካለዎት **በ አስተርጓሚ እርዳታ** ማብራሪያዎችን መጠየቅ ይችላሉ።

ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና ብቻዎን የሚጓዙ ከሆነ ወዲያውኑ ለባለሥልጣናት ወይም በታው ለሚገኙት


የሰብአዊ ድርጅቶች ያሳውቁ ። ብቻቸውን ጣሊያን የሚገቡ ታዳጊዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የመጠበቅ መብት አላቸው፣ እንዲሁም በጣሊያን የመኖር እና የሚያግዞት ሞግዚት የማግኘት እንዲሁምጣልያን እንደደረሱ ለእነሱ በተዘጋጁ ቤተ ተቋማት መስተናገድ መብትም አላቸው።

በተጨማሪም የጤና ችግሮች ካለቦት ወይም ሌላ ዓይነት ፍላጎት ካለዎት ወዲያውኑ እዛ ላሉ ለባለሥልጣናቱ ያሳውቁ ወይም ደግሞ ለሰብአዊ ድርጅቶች ማቅረብ ይችላሉ።




## 2. ወደ ሂደቱ መድረስ

ህይወትህ ወይም የቤተሰብህ አባላት አደጋ ላይ ስለሚወድቁ ወደ ሀገርህ ለመመለስ ከፈራህ ጥበቃን የመጠየቅ መብት አለህ።
ምንም አይነት ዜግነት ከሌልዎት እና ህይወትዎ ወይም የቤተሰብዎ አባላት ህይወት አደጋ ላይ ስለሆነ አሁን ወደሚኖሩበት ሀገር ለመመለስ ከፈሩ ጥበቃ የመጠየቅ መብት አለዎት።
በዘርህ፣ በዜግነትህ፣ በጎሳ አባልነትህ፣ በሀይማኖትህ ወይም በፖለቲካዊ አመለካከትህ ምክንያት ከተሰደዱ ፣ ስደትን ከፈራህ ወይም የአንድ የተለየ ማህበረሰብ አባል ከሆንክ እና ለጥቃት ወይም ለባርነት የመጋለጥ ፍርሀት ይደርስብኛል ብለህ ከፈራህ ወይም ሞት ይፈረድብኛል ወይም ያሰቃዩኛል የሚል ፋርሃት ካለህ ፣ ወይም ከጦርነት ቀጠና የመጣህ ከሆነ ጥበቃ እንዲደረግልህ መጠየቅ ትችላለህ።



ወደ ሀገርህ የመመለስ ፍራቻህን ከገለጽክ በኋላ ለባለሥልጣናቱ እንደ ጥገኝነት ጠያቂ ትቆጠራለህ።
በዚህ ደረጃ ካስፈለገዎት በእንግዳ መቀበያ ማእከል እንዲስተናገዱ መጠየቅ ይችላሉ።
የጥገኝነት ጥያቄዎን ለመመዝገብ የጣሊያን ፖሊስን ማነጋገር አለብዎት። ከዚያ በሃላ ጥያቄዎ የመገምገም ተግባር ላለው ልዩ ኮሚሽን ይተላለፋል።




የፖሊስ ኢሚግሬሽን ቢሮ ከቋንቋዎ አስተርጓሚ ጋር በመሆን C3 የሚባል ቅጽ እንዲሞሉ ይረዳዎታል፣ እሱም እንደ ብሔረሰብዎ፣ ቋንቋዎ፣ ሃይማኖትዎ ያሉ አንዳንድ ተጨማሪ ዝርዝር ግላዊ መረጃዎችን የያዘ ነዉ።
በዚህ ደረጃ ወደ አውሮፓ የወሰዶት ጉዞ እንዴት እንደነበረ፣ ስቃይ ከደረሰብዎ፣ የአካል ጉዳት፣ ጥቃት እና እስራት በሀገርዎ ወይም በጉዞ ወቅት ደርሶቦት እንደሆነ ፣ የፖለቲካ ቡድን አባል ከሆንክ፣ በጣሊያን ወይንም በ አውሮፓ የቤተሰብ አባል ካሎት እና ከእርስዎ ጋር ሰነዶች ካሉ ይጠየቃሉ።

የጤና ችግሮች ወይም ልዩ ፍላጎቶች, የተለየ አስፈላጊ ነገሮች ካሉዎት አሁን እና በማንኛውም የሂደት ጊዜ ማሳወቅ ይችላሉ።
በመሆኑም በከፋ በሽታ ፣ የአእምሮ ጭንቀት፣ ወይም ማሰቃየት፣አስገድዶ መደፈር ወይም ሌላ ከባድ የስነ-ልቦና፣ የአካል ወይም ወሲባዊ ጥቃት ደርሶብሽ ከሆነ በቂ እርዳታ እና ልዩ አገልግሎት የማግኘት መብት አልዎት።

በዚህ ደረጃ, ጥበቃን የሚጠይቁበትን ምክንያቶች በግልፅ ያብራሩ። እነዚህን ምክንያቶች በጽሁፍ ለማቅረብም አማራጭ አለዎት።

በመጨረሻም፣ የሚነገሩዎትን መረዳት እና መግለጫዎችዎ በትክክል መዘገባቸው መረዳት አስፈላጊ ነው። ጥርጣሬ ካለህ፣ የተነገረውን እንዲያብራራ ተርጓሚውን ጠይቅ።
በቃለ መጠይቁ መጨረሻ ላይ ይህን ቅጽ እንድትፈርሙ ይጠይቁዎታል እና ቅጂ ይሰጡዎታል። በጥንቃቄ ያስቀምጡት።
ያቀረቡት ሁሉም መረጃዎች በከፍተኛ ሚስጥራዊነት ይያዛሉ እና ለትውልድ ሀገርዎ ባለስልጣናት ወይም ለሶስተኛ ሀገሮች ሊጋሩ አይችሉም።

በአንዳንድ ሁኔታዎች የጥበቃ ጥያቄዎ አጭር ጊዜ በሚወስድ ልዩ ሂደት ሊገመገም ይችላል። እንዲሁም የጤና ችግሮች ወይም በልዩ ሁኔታ ሚታይ ፋላጐቶች ካጋጠሙዎት ማመልከቻዎ ቅድሚያ የማግኘት መብት አለዎት።
ያስታውሱ፣ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ወደ ማዕከሉ የህግ ኦፕሬተር ወይም የኢሚግሬሽን ቢሮ በመሄድ መጠየቅ ይችላሉ።






በከባድ ሕመም ወይም የአእምሮ ጭንቀት, ወይም ስቃይ, አስገድዶ መድፈር ወይም ሌሎች ከባድ የስነ-ልቦና, አካላዊ ወይም የ ፆታ ብልግና ዓይነቶች ከተሰቃዩ በቂ ድጋፍ እና ልዩ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አልዎት።



### ጥበቃ


እንደ ጥገኝነት ፈላጊ እንደመሆንዎ መጠን, ፈቃድ እንዲኖር እና ማመልከቻዎ እንዲመረመሩ በሚጠብቁበት ጊዜ በልዩ ማእከል ውስጥ መኖር መብት አልዎት።
ያስታውሱ ጥገኝነት ፈላጊዎች እስካሉ ድረስ ከጣሊያን ክልል መውጣት አይችሉም።
C3 ከጨረሱ ከሁለት ወራት በኋላ በጣልያን ሃገር በመደበኛነት የመሥራት መብት አለዎት።
ያስታውሱ፣ በሂደቱ በሙሉ፣ UNHCRን፣ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲን ወይም ሌላ የሚያምኑትን የጥገኝነት ኤክስፐርት ድርጅት የማነጋገር መብት አለዎት።



አስታዉሱ፣ ጥገኝነት ጠያቂ እስከሆኑ ድረስ ከጣልያን ግዛት መውጣት አይችሉም።

## 3. የደብሊን ደንብ

እዚህ ሀገር ውስጥ እራስዎን ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ እርስዎን የመጠበቅ እና ስለዚህ የጥበቃ ማመልከቻዎን የመመዝገብ ተግባር ያለው የጣሊያን መንግስት ነው።
በአጠቃላይ የጥገኝነት ጥያቄውን የመገምገም ሃላፊነት ያለው ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አውሮፓ የገቡበት ሀገር ነው። ነገር ግን፣ በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ ወይም በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት የተሰጡ ሰነዶች ካሉዎት፣ ማመልከቻዎ በዚህ ሌላ ሀገር ሊመረመር ይችላል፣ በህጋዊ እና በደህና ይተላለፋሉ። ነገር ግን፣ በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ ወይም በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት የተሰጡ ሰነዶች ካሉዎት፣ ማመልከቻዎ በዚህ ሌላ ሀገር ሊመረመር ይችላል፣ እርሶም ወደዛ ሃገር ህጋዊ በሆነ መንገድ ደህንነቶ ተጠብቆ ይተላለፋሉ።
በዚህ ምክንያት በሌላ የአውሮፓ ሀገር ውስጥ የቤተሰብ አባል ካለዎት በተቻለ ፍጥነት ለባለስልጣኖች ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።



ይህ አሰራር **"የዱብሊን አሰራር"** ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የጥገኝነት አሰራርዎ የሚካሄድበትን ሀገር የመለየት ብቸኛ አላማ አለው ነገር ግን ጥበቃ የጠየቁበትን ምክንያት አይመለከትም። የዱብሊን አሰራር ለሁሉም የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት እና እንዲሁም ለኖርዌይ፣ አይስላንድ፣ ስዊዘርላንድ እና ሊችተንስታይንን ይመለከታል።

